# ለአረጋሽ እርዳታ?

ኢትዮጵያ በላይ ethiobelay@gmail.com

*ለአቶ ተክሌ፥ ለልጅ ተክሌ፥ ለአለቃ ተክሌ ሰላምታዬ ባለህበት ይድረስህ። በተለያዩ አጋጣሚዎች የምታቀርባቸውን ጽሁፎች ስመለከት የተለያዩ ማዕረጎችን የተሸከሙ በመሆናቸው የትኛውን እንደምጠቀምበት ስለተቸገርኩ ለዛሬ በሁሉም ጠርቼሃለሁ። አያስቀይምህም ብዬም አምናለሁ።*

*ከላይ እንደገለፅኩልህ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የምታቀርባቸውን ፅሁፎች እከታተላለሁ። ከሞላ ጎደል ሲያስቁኝ፤ ሲያስደስቱኝ፤ ሲያስገርሙኝም ነበር። የዛሬው ግን በጣም ስለደነቀኝ እኔም የልቤንና የተሰማኝን ልገልጥልህ ተገደድኩ። ሆኖም ግን የዚህን አገር ኑሮ ስለምታውቀው ጊዜ በማጣት ለመፃፍ ካሰብኩበት ጊዜ ትንሽ በመዘግየቴ ይቅርታ ይደረግልኝ።*

*እሁድ መጋቢት 26 ቀን 2002 ዓም የአድዋዋን ወይዘሮ አረጋሽን "በገንዘብ ለመርዳት" በቫንኩቨር ካናዳ የምታደርጉትን እንቅስቃሴ በሚመለከት የተፃፈውን አነበብኩት። መገረም ብቻ ሳይሆን ደነቀኝ። ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ለነፃነታችን፤ ለመብታችን ራሳቸውን አሳልፈው እስከመስጠት ድረስ ከፍተኛ ትግል እያደረጉ ባሉበት በዚህ ከባድ የፍልሚያ ሰዓት፤ የእርዳታ እጃችንን የምንዘረጋላቸው እነማን እንደሆኑ ልቦናችን እያወቀው በፍፁም ከአንተና አንተን ከመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን በማይጠበቅ ሁኔታ የወያኔ ቀኝ እጅ የነበረችውን ወንጀለኛ በአሁኑ ሰዓት መደገፍ ለምን አስፈለገ? በዚህ ባለንበት የነፃ ዓለም የፈለግነውን ለማድረግ ብዙም የሚያግደን ኃይል ስለሌለ ፈልገህ የምታደርገውን አቁም ለማለት የሚደረግ፤ መብትህን የመጋፋት ጥያቄ አለመሆኑን ትረዳልኛለህ ብዬ አምናለሁ። በሌላ በኩል ግን ጤነኛው አእምሮአችን የሚደረገውንና የማይደረገውን በመምረጥ እንዲረዳን እድሉን ልንሰጠውም ይገባል እላለሁ። ሆኖም ልጅ ተክሌ ከአንተ የምጠብቀው አለነበረምና አዘንኩ።*

*ለመሆኑ ለአንተና ለመሰሎችህ አረጋሽንና ሰዬን ከመለስ የሚለያቸው ምን ይሆን? ዛሬ መለስ ዜናዊ በህግ መድረክ ላይ የሚጠየቅባቸው ወንጀሎች ሁሉ አረጋሽና ሰዬም የሚጠየቁባቸው ናቸው። አረጋሽና ሰዬ እንደጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ናቸው፤ ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊመሩ ይችላሉ፤ እኛም አላማቸውን በመደገፍ በገንዘብም ሆነ በተለያዩ መንገዶች ልንረዳቸው ይገባናል ካልክ ግን እውነቱን ልንገርህ ወንድሜ ኢትዮጵያ ሀገራችንና ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ለዚህ ሁሉ ዓመታት በነዚህ ዘረኞች ምክንያት ያዩትንና የደረሰባቸውን በደልና ሰቆቃ መካድ እንደሆነ እንድታውቀው እፈልጋለሁ። "የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ በድዬሃለሁና ይቅር በለኝ"ን የማያውቁትን ጠርነት ፈጣሪዎችን በጥንቃቄ መያዝ እንዳለብን ባምንም ከኢትዮጵያና*

*ከኢትዮጵያውያን ፍላጎት ውጭ ኃይላቸውንና ጉልበታቸውን በመጠቀም የቀሙት ከበቂ በላይ የሆነ ሀብትና ንብረት ስላላቸው ከኛ የሚፈልጉ አይመስለኝም። ስለዚህ ልጅ ተክሌ አንተ የተቸገርከው አንሶህ ለፍቶ አዳሪወን የቫንኩቨርን ህዝብ ባታስቸግር ጥሩ ይመስለኛል።*

*ውድ ተክሌ፤ ከኔና እኔን ከመሰሉት በበለጠ የመለስ ዜናዊንና የነአረጋሽን እውነተኛ ገፅታ በቅርብ የመመልከት ዕድሉ የገጠመህ ይመስለኛል። መለስ ዜናዊና ተባባሪዎቹ በስጋዊ ህይወታችን ልናገኘው የሚገባንን መብትና ነፃነት ብቻ አይደለም የነፈጉን። በመንፈሳዊ ህይወታችን እንኳ እናገኛለን ብለን የምናምንበትን መንፈሳዊ የተስፋ እንጀራችንን ነው የቀሙን። በዚህም ምክንያት ዛሬ መለስ ዜናዊና አባ ገብረመድህን የሚያስተዳድሯት ቤተክርስቲያን እንኳ አንተንና ጓደኞችህን መጠለያ ከልክላ ለመለስ ዜናዊ ወታደሮች አሳልፋ መስጠቷን የምትዘነጋውና አስታዋሽ የምትሻለት የሩቅ ጊዜ ትዝታህ አይመስለኝም።*

*ኢትዮጵያን በማጥፋት ድብቅ ዓላማ ተሞልተው ለስልጣን የበቁት ዘረኞች ለረጅም ዓመታት ይህንን እኩይ የሆነ አላማቸውን ተግባራዊ ሲያደርጉ ዓላማቸው "ኢትዮጵያ" የሚል ሳይሆን "ታላቂቷ ትግራይ" የሚለው እንደነበረ ዛሬ ላንተ ብነግርህ ለእናቷ ምጥ አስተማረች ይሆንብኛል። በዘረኛው ፓርቲያቸው ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ ለረጅም ዓመታት ተቀምጠው የነበሩት አረጋሽ አዳነና ሰዬ አብርሃ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ለተፈፀመው ወንጀል ሁሉ ተጠያቂዎች ናቸው። እኔ፤ እንኳን በመለስ ዜናዊ ዙሪያ ለዓመታት አብረውት ሲወጉን፤ ሲያቆስሉንና ሲገሉን የነበሩትን፤ ዛሬም ደግሞ ያሉትን የኢሃዴግ አባላት ቀርቶ በዘረኝነት ጥቅም ታስረው ሀገራቸውና ወገናቸው ሲደማ ዝም ብለው የተመለከቱት የትግራይ ተወላጆች እንኳ ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍርድ ነፃ ይወጣሉ ብዬ አልገምትም። መስቀለኛ መንገድ ላይ ያሉ በርካቶች ናቸው። ዛሬ ግን "እመቺነቱን" እያየን መገለባበጥ የምንችልበት ሁኔታ ላይ ያለን አይመስለኝም። የኢትዮጵያ ጉዳይ የከፋ ሁኔታ ላይ እንደሆነ ሁላችንም የተረዳነው ይመስለኛል።*

*ለኔ ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ፍርድን የሚያዩበትና የሚሰጡበት ሰዓቱ ሩቅ የሚሆን አይመስለኝም። ነፍሰገዳይና ወንጀለኛ ሁሉ በጥፋቱ ለፍርድ የሚቀርብበት ያ ቀንም ቅርብ ነው የሚል ህልም አለኝ። ስለዚህ አረጋሽና ሰዬ ዛሬ እንደገና ወንበር ለመያዝ ከመነሳታቸው በፊት ራሳቸውን በራሳቸው ለፍርድ አቅርበው፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈርድባቸውን ተቀብለው ሲፀዱ ይመስለኛል ድጋሚ ወንበር ለመጠየቅ ብቁ የሚሆኑት። ወንጀላቸው የሚያደርስባቸው ቅጣት ደግሞ ለመቼውም ህዝብን ለመምራት ብቁ የሚያደርጋቸው አይመስለኝም።*

*ወንድሜ ተክለሚካኤል፤ ዛሬ በዚህ በሰሜን አሜሪካም ሆነ በሀገራችን በኢትዮጵያ ጽህፈት ቤታቸውን ያደረጉ ብዙ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። በእውነቱ ዓላማህ ዘረኛውን የወያኔ መንግስት*

ለመጣል ከሆነ አረጋሽን እዛው ለመለስ ተዋትና በእሳት ብናነዳቸው እንደወርቅ ጥርት ብለው የሚወጡትን እውነተኛዎቹን የኢትዮጵያን የአብራክ ክፋዮች አብረን ተባብረን ተደጋግፈን ለድል እንድናበቃቸው እጋብዝሃለሁ።

በመሰረቱ አረጋሽ አዳነም ሆነች ሌሎቹ ጓደኞቿ ለማስመሰል ካልሆነ በስተቀር ከኛ እርዳታ የሚፈልጉም አይመስለኝም። የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር በእርዳታ ስም ይገባ የነበረውን ገንዘብ ለግል ጥቅም ስለማዋሉ ከሰሞኑ የቢቢሲ ሪፓርት ሌላ መረጃ የሚያስፈልግህ አይመስለኝም። የኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ እያለቀ ባለበት በዚያን ሰዓት ለተደረገው ምዝበራ ደግሞ ተጠያቂ ከሚሆኑት ከፍተኛ የወያኔ መሪዎች መካከል አንዷ አረጋሽ አዳነ ነች። ሥልጣን ከያዙም በኋላ ሀብትና ንብረታቸው እንዴት እያደገ እንደሄደ አልነግርህም "ለቀባሪው አረዱት" ይሆንብኛልና። ጥረው፤ ግረው፤ ለፍተው ያገኙት ሀብት ነው የምትለኝ ከሆነ ደግሞ የእኔም የአንተም የሁላችንም እናትና አባቶች እና ዘመዶቻችን በሙሉ እድሜ ልካቸውን ሲሰሩ ነበር የምናውቃቸው ግን ምንም ጠብ ሳይልላቸው ይኸው ኑሯቸውን እየገፉት ነው። የወያኔን ውርንጭላዎች ለመርዳት ለፍቶ የሚያድረውን የቫንኩቨር ህዝብ ማስቸገር ያለብህ አይመስለኝም። ሌሎቹን የፖለቲካ ድርጅቶች ለመርዳት ፍላጎቱ ከሌለህ እንኳ፤ አረጋሽና ጓደኞቿ በፈጠሩት የተያያዘ ችግር ምክንያት ዛሬም ዳቦ እያለ በማለቅ ላይ ያለውን ህዝብ መርዳት የሚሻል ይመስለኛል።

በወያኔ ኢህአዲግ የዘረኝነት መርዝ እንዳያልቅ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን በመቆም ክቡር ህይወታቸውን ያጡት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ፤ በወያኔ ፖለቲካ ከስራ ገበታቸው እንዲወገዱና እንዲሰቃዩ ቢደረጉም እንኳ ያለማቋረጥ ዘረኝነትን በመቃወምና የኢትዮጵያን ታላቅነት በማብሰር ላይ እያሉ ህይወታቸው ያለፈው አለቃ አያሌው ታምሩ፤ ከልጇ ተነጥላ ለኢትዮጵያውያን ነፃነት ስትል በእስር የምትማቀቀው ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸውና እስከ ነፃነት ድረስ የሚጮኸውን የነዚህ ጀግኖቻችን ድምፅ መለስ ብለህ በማሰብ የእርዳታውን አቅጣጫ እንድትቀይር አሳስብሃለሁ።

ከዚህ ባሻገር ግን መለስን ለመጣል ሌሎች ወንበዴ ወንጀለኞችን መደገፍ የሚለው፤ የአንተንም የደጋፊዎችህንም ማንንነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይመስለኛል። አንተስ ተክሌ ምን ይመስልሃል? ?